ማዕተብ

Telegram
@Deacon_abeselom

Facebook
Abeselom Dinkalem

INSTAGRAM
deacon_abeselom

YouTube
ማዕተብ

tiktok
Abeselom Dinkalem

ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፥
በበጎነትም እውቀትን፥ በእውቀትም ራስን መግዛት፥ ራስንም በመግዛት መጽናትን፥
በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፥ እግዚአብሔርንም በመምሰል
የወንድማማችን መዋደድ፥ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ።

2ኛ ጴጥ 1:7

ለምን ትመታኛለህ?

ጌታችን ከተጠመቀ በኋላ የአይሁድ ፋሲካ ለሦስት ጊዜ ተከብሯል። የመጀመሪያው ፋሲካ ጌታችን ቤተ መቅደሱን ያጸዳበትና በቤተ መቅደስ ሲሸጡ ሲለውጡ የነበሩትን ያስወጣበት ሲሆን በመጨረሻው ፋሲካም ስሞን እንዲሁ ለሁለተኛ ጊዜ ቤተ መቅደሱን አንጽቶ ከፋሲካው ማግሰት ተሰቅሏል። በሁለቱ ፋሲካዎች መካከል በነበረው ፋሲካ ደግሞ ጌታችን ወደ ቤተ ሳይዳ መጣ።

ቤተ ሳይዳ የመጠመቂያው ሰፍራ ሰም ሲሆን ከአጠገቡ

ደግሞ በጎች በር ነበር። (የበጎች በር በአሁኑ ሰዓት የቅዱስ እስጢፋኖስ (ለወግሩት ያወጡበት) በር እና የአንበሳ በር ተብሎም ይጠራል) እንደሚታወቀው ዘመነ ኦሪት በግ መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርብበት ነበር። ስለዚህ በዚያ በር መሥዋዕት ሆነው የሚቀርቡ በጎች የሚገቡብት ነበር። በጎቹ ነውር እንደሌለባቸው ማለትም ቀንዳቸው እንዳልከረረ ፣ ጥፍራቸው እንዳልዘረዘረ፣ ጠጉራቸው እንዳላረረ እያገላበጡ የሚጠኑበት ፣ የአንድ ዓመት ተባዕት/ወንድ/ መሆናቸው የሚታይበት ሥፍራ ነው። ይህን መስፈርት አሟልተው ያለፉ በጎች ለመሥዋዕትነት ሲቀርቡ ለዚህ ብቁ ያልሆኑትን ግን ለይተው ፣ በአለንጋ እየገረፉ ያሰወጡአቸዋል።

በቤተ ሳይዳ የጌታ መልአክ ወደ መጠመቂያዩቱ ወርዶ ውኃውን አንዳንድ ጊዜ ያናውጥ ነበር። ይህ መልአክ በሰው ቁስል ላይ የተሾመ ፣ በበሽታም ላይ ሁሉ የተሾመወየሰሙም ትርጓሜ <እግዚአብሔር ፈዋሽ ነውወማለት የሆነ ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት አንዱ ቅዱስ ሩፋኤል ነበር።መልአኩ ውኆችን ለመቀደስ ፣ ጸሎትን ከሰው ወደ ፈጣሪ ለማድረስ ወደ ውኃው ይወርድ ነበር። ይህ እንግዲህ ውኃ በራሱ ማዳን ባይቻለውም ቅዱሳን መላእክት የነኩት እንደሆነ በረከትና ፈውስ እንደሚሠጥ የሚያስረዳን ነው። ውኃው ከተነዋወጠ በኋላ ግን መዳን የሚቻለውመጀመሪያ መግባት ሲቻል ነበር። በዚህ የጠበል ሥፍራ በነበሩ አምስት መመላለሻዎች በሽተኞች ፣ አንካሶች ፣ ዕውሮችና እግራቸው የሰለለ ብዙ ሕዝብ ይተኙ ነበር።በተለይ ደግሞ አንካሶች ፣ ዕውሮችና እግራቸው የሰለለ ሰዎች በቁጥር የሚበዙት ከሌላው በሽተኛ በተለየ እነሱ የውኃውን መንቀሳቀስ አይተው ለመግባት እንዳይችሉ ወይ

ዓይናቸው ማየት አይችልም ፤ ያም ባይሆን መንቀሳቀስ ያቅታቸዋል። ገብተውም እንኳን ቢሆን ድንገትከእነሱ ቀድሞ የገባ ሰው ካለ እነሱ ስለማይፈወሱ ከውኃው መልሶ የሚያወጣቸውም ሰው ያስፈልጋቸዋል። አለዚያ ገብተውም አውጪ አጥተው ሊቸገሩ ይችላሉ። ምናልባትም በእንዲህ ዓይነት ችግር ለባሰ ነገር የተዳረገም ሊኖር ይችላል።

ከእነሱ ቀድሞ የሚድነው እንግዲህ ሁለት ዓይነት ሰው ነው። አንደኛው በሽታው ለመንቀሳቀስ የማያግደው ሆኖ እያለ የእነሱ ይብሳል ብሎ ሳያዝን የሚገባ ነው። መቼም ሰው እንኳን ቀድሞ የገባ ሰው ብቻ በሚድንበት ሥፍራ ቀርቶ ፤ በማንኛውም ሰዓት ቢገባ በሚዳንበት የጠበልሥፍራ ከእኔ በሽታ የእገሌ ይብሳል ፤ እስቲ ቅድሚያ ልስጠውወሲል ብዙ ጊዜ አይታይም። ስለዚህ እነዚህን ደካሞች ቀድሞ የሚገባ በሽተኛ ብዙ ነው። በእንጻሩ ደግሞ ወደ መጠመቂያው ሊወረውሩት የሚጠባበቁ ዘመዶች ያሉት ፣ አለዚያም ዘመድ የሚያፈራበት ገንዘብ ያለው በሽተኛ ደግሞ ሌላው ቀድሞ ወደ መጠመቂያው የሚገባ ነው።

በዚህ ሥፍራ ለሠላሳ ስምንት ዓመታት ያህል የተኛ በሽተኛ (በግእዙ መጻጉዕ) ነበር። እንግዲህ ሠላሳ ስምንት ዓመት ማለት የጉልምስና ዕድሜ ነው።መጻጉዕ የመጣው በዐሥር ዓመቱ ነው እንኳን ብንል አሁን አርባ ስምንት ዓመቱ ይሆናል። ነገር ግን ጌታችን በኋላ የሚብስ እንዳይደርስብህ ደግመህ ኃጢአትን አትሥራ ውብሎ ስለተናገረ ከመታመሙ በፊት ለዚህ ጽኑ ደዌ

የሚዳርግ ኃጢአት ለመሥራት የሚችልበት ዕድሜ ላይ ደርሶአልማለት ነው። መቼም ክፉ ደግ በማያውቅበት ሕጻንነቱ በድሎ የልጅነቱ መተላለፍ ታሰቦበትመታመመ ብሎ መናገር ይከብዳል። ብቻይህ ሰው የአንድ ጎልማሳ ዕድሜ ያህል በአልጋ ላይ ሆኖ በቤተ ሳይዳ ተኝቶአል። ጠበል ሊጠመቅ ሲጠባበቅ በጸጉሩ ሽበት ፣ በግንባሩ ምልክት አውጥቶአል። ጌታችን ኢየሱሰ ክርሰቶሰ በቤተልሔም ግርግም ውሰጥ ሲወለድም ይህ በሽተኛ በዚሁ መጠመቂያ ሰፍራ ነበረ፡፡ ድንግል ማርያም የወለደችውን ሕጻን በበረት ውሰጥ ሰታሰተኛው ይህ በሽተኛ አልጋው ላይ ከተኛ ሰድሰት ዓመት ደፍኖ ነበር፡፡

ከሁሉ የሚያሳዝነውደግሞ ይህ ሰው አልጋው ላይ ሆኖ እጅግ ብዙ ሰዎች ሲፈወሱ መመልከቱ ነው። ከእሱ በኋላ መጥተው ከእሱ በፊት ድነው የሚሔዱ ሰዎችን ማየት እንዴት ይከብደው ይሆን? እንደሱ ብዙ ዘመን የቆዩት ሲድኑ ሲያይ ተሰፋው ሊለመልም ይችላል። በመጡ በአጭር ጊዜ ዘመደ ብዙ በመሆናቸው ብቻ የሚድኑ ሰዎችን ሲያይ ግን ልቡ በኀዘን ይሰበራል። ዓመቱ በረዘመ ቁጥር ተሰፋ ቆርጦ ቤተ ሳይዳን ቤቴ ብሎ ከመኖር በሰተቀር ምንም የሚታየው ነገር አይኖርም። እግዚአብሔርን በመከራው ውሰጥ ተሰፋ እያደረገ ይጽናናል አንዳንል ደግሞ እንደ ጻድቁ ኢዮብ ወይም እንደ በሽተኛው አልዓዛር ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት የነበረው ቢሆን ኖሮ መቼ ለዚህ በሽታ የሚዳርገው ኃጢአትይሠራ ነበር? ሰለዚህ በቃለ እግዚአብሔር ይጽናናል ማለትም ያሰቸግራል።ያም ሆነ ይህ ይህ ሰው እጅግ ተሰቃይቶ ነበር።

ጌታችን የዚህን ሰው ችግር ብቻ ሳይሆን ብዙ ዘመን እንደዚህ እንደነበረ ያወቀው ማንም ሳነግረው ነበር። በሽታውን ከነመንሥኤው አስቀድሞ ያውቃልና ወደዚህ የብዙ ዓመታት በሽተኛ መጣና ልትድን ትወዳለህን?› አለው። ጌታችን የሚፈልገው ይህንን ሰው መፈወስ እንጂ የራሱን ማንነት ማሳየት ስላልነበረ ‹ላድንህ ትወዳለህን?› አላለውም። በዚያ ላይ ይህ ሰው የጌታን ማንነት አያውቅም። ጌታችን ስታምኑብኝ ብቻ ነው የምፈውሳችሁ፣የሚል አምላክ አይደለም ፣ ለሁሉ ፀሐይን የሚያወጣ ፣ ለሁሉ ዝናምን የሚያዘንም አምላክ ይህንን ሰውም ለመፈወስ እስኪያምነውም አልጠበቀም።

ይህ በሽተኛ ልትድን ትወዳለህን?› ሲባል የሠጠው መልሰ እጅግ የሚያሰገርም ነው። እንደሚታወቀው በሽታ አመል ያጠፋል። በሽታው በቆየ ቁጥር ደግሞ መራር ያደርጋል። ሰዎች በበሽታ ሲፈተኑ በሰው በፈጣሪም ላይ ብዙ የምሬት ንግግር ሊናገሩ ይችላሉ። ጌታችን ልትድን ትወዳለህን?›ብሎ ሲጠይቀው ታዲያ መዳን ባልፈልግ ጠበል ቦታ ምን አስቀመጠኝ? እያየኸኝ አይደል.. › ወዘተ ብሎ ብዙ ያለፈ ንግግር ሊናገር ይችል ነበር። ይህ ሰው ግን ምንም የምሬት እና የቁጣ ቃል አልተናገረም። ጌታችንም ሲያናግረው በጨዋ ሰው ደንብ ጌታ ሆይ..›ብሎ ነው የመለሰለት። በዚህ ሁኔታው ትሑት ሊባል ይችላል።

ነገር ግን የመለሰው የተጠየቀውን አይደለም። ጥያቄው

‹ልትድን ትወዳለህን?› የሚል ከሆነ መልሱ አዎ መዳን እወዳለሁወእለዚያም እይ አልፈልግምውብቻ መሆን ነበረበት። እሱ ግን ጌታ ሆይ፥ ውኃው በተናወጠ ጊዜ በመጠመቂያይቱ ውስጥ የሚያኖረኝ ሰው የለኝም ነገር ግን እኔሰመጣ ሳለሁ ሌላው ቀድሞኝ ይወርዳል ብሎ መለሰለት።ወእንግዲህ የጌታችንን ማንነት ባይረዳውም ጌታችን በወቅቱ የሠላሳ ሁለት ዓመቱ ነበርና ‹ምናልባት ወደ መጠመቂያው ሊጨምረኝ አሰቦ ይሆናል ያም ባይሆን ግን ከተከተሉት ሰዎች አንዱን አደራ ሊልልኝ ይሆናልውብሎ አሰቦ ነበር። ሰው የለኝምውብሎ የሠላሳ ሰምንት ዓመታት ብሶቱን ተናገረ።

ሌላው ቀድሞኝ ይወርዳልውብሎ እያየ የቀደሙትን ሰዎች አሰታወሰ።

ጌታችን ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሒድውአለው። ባላሰበው ባልጠበቀው መንገድ ፈወሰው። ይህ ሰው ሠላሳ ሰምንት ዓመት ሙሉ ሲጠባበቃት የነበረችውን የቤተ ሳይዳ ጠበል ሳያገኝ ፣ በመልአኩ መውረድ ሳይሆን በመላእክት ፈጣሪ ቃል ተፈወሰ። ገባሬ መላእክት ክርሰቶሰ ራሱ መጥቶ አዳነው። ይህ ሰው እግዚአብሔር በዚህች ጠበል ካልሆነ በቀር በሌላ በምንም መንገድ ያድናል ብሎ አሰቦም አልሞም አያውቅም ነበር። ለመዳን የሚያሰፈልገው ምንድን ነው ተብሎ ቢጠየቅ የሚመልሰው ወደ ውኃው የሚጨምር ሰው እና የቤተ ሳይዳ ውኃውብሎ ነበር። ጌታችን መጻጉዕ ለሠላሳ ሰምንት ዓመታት ተሰፋ ያደረጋትን ጠበል ወይም

ደግሞ ወደ ጠበሉ የሚጨምሩትን ሰዎች ሳይጠቀም ፈወሰው። እግዚአብሔር ያለ ጠበልም እንደሚያድን ማመን ካልቻልን እምነታችን ሙሉ አይደለም። ይህ ሰው ወደ ውኃው ገብቶ ቢድን ኖሮ ጌታዬ አዳነኝወከማለት ይልቅ መዳን ይነሰኝ? ሠላሳ ሰምንት ዓመት እኮ ነው የጠበቅኩት…›› እያለ ልፋቱን ያወራርድ ነበርእንጂ ፈጣሪውን እያመሰግንም ነበር።

ጌታችን ጠበል ቦታ ያገኘውን ያለ ጠበል ፈወሰው ሲባል መቼም ጠበል መጠመቅ የማይወዱ ወይም በጠበል የማያምኑ ሰዎች ደሰ ሊላቸው ይችላል። እኛስ ምን አልን ጌታ እኮ ይህን በሽተኛ ጠበል ቦታ አግኝቶ እንኳን የፈወሰው ያለ ጠበል ነውመ ብለው ባቀበልናቸው በትር ሊሙቱንይፈልጉ ይሆናል። ሆኖም እዚሁ ዮሐንሰ ወንጌል በዘጠነኛው ምዕራፍ ላይ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ጠበል በሌለበት ሥፍራ አግኝቶትእኛ እመት (እምነት) የምንለውን አፈር በምራቁ ለውሶ ከቀባው በኋላ ሒድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብውብሎ ልኮታል። ጠበል ምንምየማያሰፈልግ ቢሆን ኖሮ ዓይነ ሰውሩን ሰው ወደ ወንዝ ወርደህ ተጠመቅ ብሎ አይልከውም ነበር። ዛሬ ለታመሙ ሰዎች ጠበል ሒዱ ብለን ሰንመክር ክርሰትና ያልገባን ፣ ክርሰቶሰን የማናውቅ የሚመሰለው ይኖራል። አሁን ባየነው ታሪክ ውሰጥ ግን ለበሽተኛው ጠበል ሔደህ ተጠመቅውብሎ የመከረው ራሱ ጌታችን ኢየሱሰ ክርሰቶሰ ነው። መፈወሰ የሚቻለው ክርሰቶሰ ጠበል ተጠመቅ ብሎ ከተናገረ ፤ የታመመን መፈወሰ የማንችለው እኛ ኃጢአተኞቹ ከንፈር ከመምጠጥ ይልቅ ሔደህ ተጠመቅ ብንል ምን እጥፍተናል? ጌታችን ሲያደርግ ያየነውን ነው።እኔን ምሰሉ ብሎ የለ እንዴ? (ዮሐ

9፡7)

በእነዚህ ሁለት ታሪኮች ግን ጌታችን ሲፈልግ በጠበል ሲፈልግ ያለ ጠበል ፤ ሲሻው በምክንያት ሲሻው ያለ ምክንያት። ሲፈልግ በጠበል ሲፈልግበህክምና ፤ ሲፈልግ በቃሉ ሲፈልግ በዝምታ ፣ ሲፈልግ በቅዱሳን መላእክቱ ሲፈልግ ያለ ቅዱሳን መላእክቱ ማዳን እንደሚቻለው እንረዳለን።

ጌታችን ለመጻጉዕ ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሒድወ ብሎ ሲነግረው ወዲውኑ ድኖ አልጋውን ተሸክሞ ሔደ። እዚህ ላይ አባታችን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳደረገው የበሽተኛውን እምነት እናደንቃለን። ራሱን መሸከም የማይችለው ይህ በሽተኛ ተነሣና አልጋህን ተሸከም ሲባልአልሳቀም። እንዴት አድርጌ ነው ደግሞ አልጋ የምሸከመውውብሎ አልጠየቀም። በፍጹም እምነት ተነሣና ተሸክሞ ሔደ። የሠላሳ ሰምንት ዓመት ጓደኛውን ፣ ሰው ሳይኖረው አብራው ኖረችውን ፣ የተሸከመችውን ባለ ውለታው የሆነችዋን አልጋ ተሸክማት አለው - ተሸክሞ ሔደ።

አንድ ሰው እንኳን ለሠላሳ ሰምንትዓመታት ይቅርና ለሠላሳ ሰምንት ቀናት እንኳን ቢታመም እንደተሻለው ተነሥቶ አልጋ አይሸከመምም። እሰከሚያገግም ድረስ በደንብ መንቀሳቀስአይችልም። ራሱን ያዞረዋል ፣ ደክመዋል። የቀረ ሕመም አያጣውም። መጻጉዕ ግን የተፈወሰው ያለ ቀሪ በሽታ (ያለ ተረፈ

ደዌ)ነበር። ስለዚህ ወዲያው ተነሥቶ አልጋውን እንዲሸከም ነገረው። መምህር ኤሰድሮስ እንዳሉት ያንን የብረት አልጋ ተሸክሞ እየሔደ የጌታን ጽንዐ ተአምራት አሳየ። ጌታችንም ከዛ በሽታ ያዳነው በነጻ መሆኑን በሚያሳይ ሁኔታ ያችን አንዲት ንብረቱንም ተሸክመህ ሒድ አለው።

መጻጉዕ የተሸከመችህን አልጋ ተሸከምተባሉ። እግዚአብሔር የተሸከሙንን እንድንሸከም የሚፈልግ አምላክ ነው። ውለታ ሳንረሳ የተሸከሙንን ወላጆቻችንን የተሸከመችንንቤተ ክርስቲያንን ፣ የተሸከመችንን ሀገራችንን እንድንሸከም ይፈልጋል። በአንዱ ሊቅ ደግሞ ዓለም እንደዚህ ናት ፤ እናት ዓለምአልጋ መጻጉዕን እንደተሸከምኩህ ተሸከመኝ አለችውውብለው ተቀኝተዋል። (ዝክረ ሊቃውንት 2)

እዚህ ላይ ጌታችን ቤተ ሳይዳ ከመጣ አይቀር ሁሉንም በሽተኛ መፈወስ ሲችል ለምን አንዱን ብቻ ፈውሶ ሔደ? ብለን ማሰባችን አይቀርም። የበለጠ የሚያሳዝነው ደግሞ ሊቃውንቱእንደጻፉት የቤተ ሳይዳው መጠመቂያ ፈውስ ከዚያ በኋላ ብዙም አልቆየም። የመልአኩም መውረድ ቆሞአል። ከዚያ በኋላ በሰባ ዓመተ ምሕረትም ኢየሩሳሌም መቅደሰዋ ፈርሶአል ተመሰቃቅላለች። ወንጌላዊው ዮሐንስም የዮሐንስ ወንጌልን ሲጽፍ <<ቤተ ሳይዳ የምትባል አንዲት መጠመቂያ ነበረች፤ አምስትም መመላለሻ ነበረባት።… ብዙ ሕዝብ ይተኙ ነበር።… ከማናቸው ካለበት ደዌ ጤናማ ይሆንነበር።መብሎ በኃላፊ ኃላፊ ግሥ /past perfect tense/ ነበር።

ታዲያ ጌታችን እንዲህ መሆኑን እያወቀ ምነው መጻጉዕን ብቻ ፈውሶት ሔደ? ቢባል የፈወሰው እሱን ብቻ አይደለም።እሱን በሥጋ ቢፈውሰውም ተአምራቱን አይተው በማመናቸው በነፍሳቸው የተፈወሱ ይበዛሉ። ሕሙማነ ሥጋን በተአምራት ሕሙማነ ነፍሰን በትምህርት እየፈወሰወእንዲሉ አበው በዚያ ሥፍራ በሥጋ ታመው በነፍሳቸው አምነው የዳኑ ብዘዎች ናቸው። የጌታችንና የእርሱ አካል የሆነች የቅድሰት ቤተ ክርሰቲያን ዋነኛ ሥራዋ ነፍሰን መፈወሰ እንጂ ሥጋዊ በሽታን መፈወሰ ብቻ አይደለም። ለዚህ ነው እንጂ ጌታችን ሰው ሆኖ ይህችን ምድር በእግሩ ሲረግጥ በሽታ እንዳይኖር ያደርግ ነበር። ቅዱሰ ባሰልዮሰ በመሰቀል ላይ በቆሰልኸው ቁሰል ከኃጢአቴቁሰል አድነኝወብሎ እንደጸለየ እኛም የዞወትር ልመናችን ለሚከፋው ለነፍሳችን በሽታ ነው።

የጌታችን መምጣት ዋነኛ ዓላማ ለነፍሰ ድኅነት ነው ፡ ፡ ይህ ማለት ግን ለሥጋ አልመጣም ማለት አይደለም ፡ ፡ ጌታችን <<ኃጢአተኞችን ለንሰሐ ልጠራ መጣሁ እንጂ ጻድቃን ልጠራ አልመጣሁምወ ከእሰራኤል ቤት በቀር ለአሕዛብ አልተላክሁምወ ሲል ለጻድቃን አይገደኝም ፣ ለአሕዛብ አላሰብም ማለቱ እንዳልነበር ሁሉ ለነፍሰ ድኅነት ቅድሚያ ሠጥቶአል ማለት ለሥጋ አይገደውም ማለት አይደለም።

በመጻጉዕ ታሪክ ውሰጥ ብዙ ቀሪ ነጥቦች ቢኖሩም ሁለት ነገሮችን ብቻ እናንሣና ይህችን አጭር ጽሑፍ እንግታ። ይህ ሰው

ተፈውሶ አልጋውን ተሸክሞ ሲሔድ ሰንበት ለሰው ድኅነትእንደተፈጠረች ያልተረዱ አይሁድ በቁጣ ነደዱ። ሰንበት ነው አልጋህን ልትሸከም አልተፈቀደልህምመአሉት። ልብ አድርጉ ይህሰው በቤተ ሳይዳ ሠላሳ ስምንት ዓመታት ሙሉ ሲማቅቅ እንደኖረ የሰውን ገመና አዋቂ ነን ባዮቹ አይሁድ ይቅሩና ቤተ ሳይዳን የረገጠሰው ሁሉ ያውቃል። ላለፉት ሠላሳ ስምንት ዓመታት ወደዚያች የመጠመቂያ ስፍራ ሲሔዱ ያም ባይሆን በጎች ታጥበው ተመርጠው ወደሚገቡብትወደ በጎች በር ሲያልፉ ይህን በሽተኛ በአልጋው ተጣብቆ ሳዩት አይቀሩም። አሁን ግን ከአልጋው ተነሥቶ የተሸከመችውን እ

ልጋ ተሸክሞበአደባባይ ሲያዩት የጠየቁትን ጥያቄ ተመልከቱ። <<እንኳን ለዚህ አበቃህ ፤ ዛሬ መልአክ ወረደ ማለት ነው?>> <<እሰይ ልፋትህን ቆጠረልህ!>> ያለው የለም። የተናገሩት አንድ ዐረፍተ ነገር ነው። ሰንበት ነው አልጋህን ልትሸከም አልተፈቀደልህምመየሚልብቻ! በአይሁድ ዓይን ድኖ ሠላሳ ስምንት ዓመት የተኛበትን አልጋ ከመሸከሙይልቅ ሰንበት ማፍረሱ የሚያሰደንቅ ትልቅ ዜና ነው።

መጻጉዕ ያዳነኝ ያ ሰው አልጋህን ተሸከም አለኝወ አላቸው። እሰቲ በደንብ አሰተውሉ። እነዚህ ሰዎችይህን በሽተኛ ፈጽሞ አያውቁትም ነበር እንበል። እንደዛ ከሆነ ያዳነኝ ሰውወ ሲላቸው ከምንድን ነው የምትድነው? ምን ሆነህነበር? ከየት ነው የመጣኸው?> ይሉ ነበር። ነገር ግን ጠንቅቀው ያውቁታል። መዳኑን

ማየት አልፈለጉም እንጂ ማን እንደሆነ ጠንቅቀውያውቁታል። ከዚያም   ያዳነኝ ያ ሰው አልጋህን ተሸከም አለኝ>>ሲላቸው <<አልጋህን ተሸክመህ ሒድ ያለህ ሰው ማን ነው?>>ብለው ጠየቁት። እስቲ ጥያቄና መልሱ ውስጥ ያለውን ሽሽት እንመልከት። <<ያዳነኝ ሰው አልጋህን ተሸከም አለኝ>>ለሚለው መልሰተኪታዩ ጥያቄ   ማን ነው ያዳነህ?> የሚል ነበር። እነሱ ግን የጌታንየማዳን ሥራ ላለመስማት ጆሮአቸውን ደፍነው ስለነበር አልጋህን ተሸከም ያለህ ማን ነው?> አሉ። የማዳኑን ሥራ እያዩ ከማመንይልቅ መከራከር ፣ ከማድነቅ ይልቅ የትችት ሰበብ መፈለግ እንግዲህጌታን የሰቀሉ የአይሁድ ጠባይ ነው።

የመጨረሻው ነገር መጻጉዕ ከዚህ በኋላወደ አይሁድ ሄዶ ጌታን መክሰሱና ለጌታ ሞት የመማከራቸው ምክንያት መሆኑ ነው። ይህ ሰው የሚብሰ እንዳይገጥምህ ደግመህ ኃጢአትንአትሥራወ ብሎ ጌታ ቢያሳሰበውም አልሰማም። ጌታ በተያዘበት በምሴተ ሐሙሰ ለሊቀ ካህናቱ አግዞ ጌታችንን በጥፊ መታው። ጌታችንም   ክፉ ተናግሬ እንደሆነ ሰለ ክፉ መሰክር መልካም ተናግሬ ከሆነ ግን ሰለምን ትመታኛለህ?>> አለው። (ዮሐ 18:23) <<አልጋህን ተሸክመህ ሒድ ከማለት በቀር ክፉቃል ተናግሬህ ከሆነ መሰክርብኝ ፤ የተናገርኩህ መልካም ሆኖ ሳለ ሰለምን ትመታኛለህ>>ማለቱ ነበር። ጌታችን በማግሥቱ ያ ሁሉጅራፍና ግርፋት ሲደርሰበት አንድም ጊዜ   ለምን ትመታኛለህ>>ብሎ አልተናገረም። የመጻጉዕ ጥፊ ይህን ያህል ዘልቆ የተሰማውለምንድር ነው?

የመጀመሪያው ምክንያት ከቤተ ሳይዳ ከበጎች በር ጋር የተያያዘ ነው። ጌታችን የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ነው። በበጎች በር አልፎ የመጣውንጹሐ ባሕርይ እንደሆነ ለማስረዳት ነበር። ለዚህም ንጽሕናው ዋነኛው ምስክር ፈውሰን የሠጠው ይህ በሽተኛ ነበር። እሱ ግን መታው።   በቤተ ሳይዳ ክፉ ቃል ተናግሬህ ከነበር መስክርብኝወ ማለቱ   ነውርየሌሉብኝ ፣ ለመሥዋዕት የተዘጋጀሁ በግ ነኝ ለምን ትመታኛለህ?› ማለቱ ነበር። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ከሮማውያን ግርፋት በላይለጌታ ዘልቆ የሚሰማው ባዳነው ሰው መመታቱ ስለሆነ ነው። ውድ አንባቢያን መጻጉዕ ከሠላሳ ስምንት ዓመት በሽታ ብቻ ዳነ ፣ እኛግን የዳንነው ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት በሽታ ነበር። ጌታችን እኛን ያሰነሣን ከሲኦል አልጋ ነው። ከሌላው ሰው ይልቅእግዚአብሔር የእኛ ዱላ ይሰማዋል። ይህም ዱላ ኃጢአታችን ነው። እግዚአብሔር ዛሬም ድረሰ ለእያንዳንዳችን ይጠይቃል።   ለምን ትመታኛለህ?››

እናመሰግናለን!

በአገልግሎታችን ከተደሰታችሁ ምስጋናን ሁሉ ጸጠቅልላችሁ

ለእግዚአብሔር ስጡ ።

ለወዳጆቻችሁ ሁሉ ያጋሩ

ማዕተብ

https://t.me/bale_maeteb

abeselomdinkalem78@gmail.com

telegram/facebook/youtube/Instagram